# ኒዮ- ኮሎኒያሊዝምና አፍሪካ

በሲሳይ ጌቱ

እናት አህጉር ይሏታል። የራሷ ዘመን አቆጣጠር ያላት፣ የነፃነት ተምሳሌት ሀገርና የቀደምት የሰው ዘር መገኛ አህጉርም ነች። የሰው ልጆች መኖር ከጀመሩባት ከአምስት ሚሊዮን አመት በላይ ሆኗታል። በህንድ ውቅያኖስ፣በቀይ ባህር፣ በአትላንቲክ ውቅያኖስና በሚዲትራንያን ባህር ዙሬዋን ተከባለች። የስልጣኔ መነሻና ተምሳሌትም ነች። ድንቅ ምድር፤ አፍሪካ።

አፍሪካ በህዝብ ብዛቷና በቆዳ ስፋቷ ከአለም ሁለተኛዋ አህጉር ነች። በአፍሪካ ውስጥ ተነግሮ ያላለቀ ተቆጥሮ ያልተጨረሰ እምቅ የተፈጥሮ ሃብትና ሰው ሰራሽ ቅርሶቿ በጣም በርካታ ናቸው። ከበረሃማ እስከ ደጋማ የአየር ንብረት፤ከረጅሙ ወንዝ አባይ እስከ ሰፊው ቪክቶሪያ ሃይቅ ፣ ከኪሊማንጃሮ ተራራ እስከ ዝቅተኛው ዳሎል ድረስ በውስጧ አቅፋለች። ከወርቅ እስከ ዩራኒየም፣ከአልማዝ እስከ ነዳጅ፣ ጥቅጥቅ ካሉት የምድር ወገብ ደኖች እስከ ሰረንጌቲ ፓርክ፣ ከሰሃራ እስከ ናሚቢያ በረሃ ድረስ በጉያዋ አቅፋ የያዘች ድንቅና ውብ አህጉር ነች።

ሰፋፊና ለም የእርሻ መሬቶች፣ያልተነኩ ማዕድናትና ርካሽ የሰው ሃበትም ይገኝባታል። የቀይ ባህር ሰርጥና ስዊዝ ካናል መገኛ ስለሆነች ከፍተኛ የንግድ መተላለፊያ ቀጠና ነች። የምትገኝበት ስልታዊ መገኛ ሁሉንም አህጉር ማስተሳሰር በመቻሏ የምዕራባዊያንን ዓይኖች አማለለች። መማለል ብቻ ሳይሆን ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ ካላቸው ጥልቅ ፍላጎት በመነሳት በተለያየ ምክንያት እጃቸውን ወደ አህጉሪቱ መላካቸውን አላቋረጡም።

ለዚህም ሲባል "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል'' እንደሚባለው ይህችን የቀደምት የስልጣኔ ባለቤት አፍሪካን የተለያየ ስም ይሰጧታል። ሲፈልጉ በማደግ ላይ ያለች አህጉር፤ ሲያሻቸው ሶስተኛዋ አለም፤ ከዚህ ሲያከፋት ደግሞ ኋላ ቀሯ አህጉር ይሏታል።

አውሮፓዊያን ለፋብሪካቸው ግብአት የሚሆን ጥሬ እቃ ስለአስፈልጋቸውና እያደገ የመጣው የኢንዱስትሪ መስፋፋት ወደ ውጭ እንዲመለከቱ አስገደዳቸው። የፋብሪካ ምርቶቻቸውን የሚያራግፉበት እንዲሁም ፋብሪካቸው ያለማቋረጥ እንዲሰራ የሰው ኃይል ፈለጉ። ቀደም ብለው በባሪያ ንግድ ያውቋት ወደ ነበረችው አፍሪካም አማተሩ። ለምሳሌ ቤልጀም በአሁኗ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ በያኔዋ ኮንጎ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በመግባት ተጠቃሚ የሆነች የመጀመሪያዋ ሀገር ነበረች።

የዚህን ሴራ ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንቃኘው ምዕራባዊያን በአንድ ወቅት የራሳቸውን ፍላጎት በአፍሪካ ላይ በኃይል ለመጫን በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ነበር። ይኸውም በቤልጀሙ ንጉስ ሊዮፖልድ II ኛ መሪነት በአሜሪካ አጋፋሪነት በ 1884/5 ዓ.ም 14 የሚሆኑ የአውሮፓ ሃገራት መሪዎች አፍሪካን ለመቀራመት በጀርመኗ ዋና ከተማ በርሊን ነበር የተሰባሰቡ። የውይይቱ አላማም አፍሪካን

በመከፋፈል/በመቀረማመት ማዳከም፣ ሀብታቸውን በመከፋፈል በአውሮፓና በምዕራባዊያን ገበያ ላይ ለማውጣትና የአፍሪካን ህዝብ በማያልቅ ችግር ውስጥ ማስገባት ነበር። በስምምነታቸው መሰረትም አህጉሪቱን እንደ ቅርጫ ስጋ በመከፋፈል የቻሉትን ያህል በዝብዘዋል።

በዚህ ምክንያት አፍሪካ ለምዕተ አመት በአውሮፓዊያን ቅኝ ግዛት መከራዋን አይታለች። አፍሪካዊያን በምድራቸው እንደሰው ሳይቆጠሩ በባርነት ማቀዋል፣ በራሳቸው ሀገር ባይተዋር ሆነዋል፣ በንብረታቸው መጠቀምና ያሻቸውን ማድረግ ምኞት ብቻ ሆኖ ቀርቷል፣ በድህነት ውስጥ እንዲማቅቁ ተደርጓል፣ ሚሊዮኖች አልቀዋል፣ሌላም ሌላ ሆነዋል። የተገላቢጦሽ አውሮፓዊያኑ የአፍሪካን የተፈጥሮ ሃብት በመሚጠጥ በአፍሪካዊያን ሀብት በልጽገዋል።

የሁለተኛው የአለም ጦርነት በተቀሰቀሰበት ወቅትም ብዙ አፍሪካዊያን ለቅኝ ገዢዎቻቸው እንዲሰለፉ ተደርገው ተሰውተዋል። የሚገርመው አውሮፓዊያኑ እያንዳንዱ በጦርነቱ የሞተውን ዜጋቸውን መዝግበው ሲያውቁ  አብረዋቸው በመዋጋት ለተሰውት አፍሪካዊያን ግን “የምናውቀው የለም” ብለው ይመልሳሉ። ሰነዶች ግን አፍሪካዊያን በማያገባቸው ጦርነት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ማለቃቸውን ይገልፃሉ።

ለአፍሪካዊያን ያልተገባና የሁለተኛው የአለም ጦርነት ማብቃት ተከትሎ ለአህጉሪቱ የምስራች የሚያሰኝ ሁኔታ ተከሰተ። ከዚያ ሁሉ እልቂት በኋላ ግን በርካታ አፍሪካዊያን የግፍ አገዛዙን  በመቃወም ለነፃነታቸው ትግል ማድረግ ጀመሩ። የቅኝ አገዛዝ ስርዓትም እተዳከመ መጣ። ምንም እንኳ ትግሉ በራሱ መራራ ቢሆንም በ1960ዎቹ መጀመሪያ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ነፃ ወጡ። ዳግም እንደዚህ ያለ አስከፊ ወረራ እንዳይፈጸም በማሰብ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ተመሰረተ። አፍሪካዊያኑ ተቀዳጅተዋል የተባለው ነፃነት ግን ሙሉ አልነበረም። የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ስሙን እየቀያየረ ቆሞ ቀረ። አለም በአንድ መንደር በተሳሰረበት በዚህ ዘመን የቀድሞዎቹ ቅኝ ገዥ የአውሮፓ ሀገራትም ሆኑ አሜሪካ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ከዘመኑ ጋር ዘምኖና ሴራ ተሸርቦ መቀጠሉ ነው።

በፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ስር የነበሩ ሀገሮች ከግማሽ ምዕተ አመት በላይ መከራቸውን እየበሉ ዛሬም ድረስ የቀጠለ መሆኑ ነው። እነዚህ ሀገራት በምድራችሁ ለገነባነው መሰረተ ልማት ግንባታ የኢንቨስትመንት ብድር ክፈሉ እየተባሉ ዛሬም ድረስ በትሪሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ይዘረፋሉ። የማዕድን ማውጫዎችን ሳይቀር በእኛ ኩባንያ ስር መውጣት አለበት በማት አሁንም በግዞት ያስተዳድራሉ። ይህን የማይቀበሉ መሪዎች እጣ ፈንታቸው ሁለትና ሁለት ብቻ ነው። አንድም ይገደላሉ፤ አለዚያ ድግሞ ህዝብን በማነሳሳት በመፈንቅለ መንግስት ስም ከስልጣን እንዲወገዱ ይደረጋል። ግድያውንና መፈንቅለ መንግስቱን መፍራት ብቻ ሳይሆን አፍሪካ ውስጥ ስልጣን የሃብት ማካበቻ ስለሆነ አብዛኛዎቹ መሪዎች የሀገራቸውን ጥቅም ከማስከበር ይልቅ በአጎብዳጅነት ዘመናቸውን ይጨርሳሉ።

መፈንቅለ መንግስት በማስነሳት የሁከትና ብጥብጥ ማዕከል ያደርጋሉ። እ.ኤ.አ ከ1950 እስከ 2022 ዓ.ም ድረስ አፍሪካ ውስጥ ከ214 በላይ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደርጓል። ከዚህም ውስጥ 106ቱ ሲሳካ 108 ሚሆነው ከሽፏል። ሱዳን ስድስት መፈንቅለ መንግስት አሳክታ 17ቱን ማክሸፍ ስትችል በኢትዮጵያም ሁለት ጊዜ ሲሳካ አምስቱ ደግሞ ከሽፏል።

መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ከጦር መሳሪያ ድጋፍ እስከ የሰው ኃይል ስልጠና ድረስ ይሰጣሉ። ሲፈልጉም ደግሞ በማዕቀብ ስም እንዳይቀጥል የፈለጉትን መሪ ሳይወድ በግድ እጁ እንዲጠመዘዝ ይደረጋል። አለፍ ሲልም በብድርና በድጋፍ ስም ሲሰጡት የነበረውን ገንዘብ ከማቋረጥ ጀምሮ የብድር መመለሻ ጊዜ አልቋል በማለት መፈናፈኛ ያሳጣሉ። ለዚህ አላማ እንደ ማስፈጸሚያ የሚጠቀሙበት ስማቸው አለም አቀፍ የሆኑ ነገር ግን የእነሱ የግል ድርጅቶችም አሏቸው። እንደ አለም ባንክ(WB)፣ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ድርጅት(IMF)፣ የአለም የጤና ድርጅት(WHO)፣ የአለም የምግብ ፕሮግራም(WFP)፣ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት(USAID)ና ሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች ይጠቀሳሉ።

ከቋንቋ እስከ ብሄራዊ ባንክ ከባህል እስከ መገበያያ ገንዘብ ድረስ የእነሱን እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ። በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ስር የነበሩት ሀገራት የትምህርትና የስራ ቋንቋቸው ፈረንሳይኛ ነው። ነባሩ ባህልና ቋንቋቸው በህይወትና በሞት መካከል ሆኖ የመሞቻውን ጊዜ ይጠባበቃል። በጅቡቲ፣ ሴኔጋልና ጋቦን ቋሚ የጦር ሰፈር ገንብታለች። በወታደራዊ ትብብር ስምም የጦር መሳሪያ ከፈረንሳይ ብቻ እንዲገዙ ይገደዳሉ።

የአሜሪካ አፍሪካ ትብብር፣ የቻይና አፍሪካ ትብብር፣ የሩሲያ አፍሪካ ትብብርና የህንድ አፍሪካ ትብብር እየተባለ በየጊዜው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሰነድ ይዘጋጃል፤ ስምምነት ይፈረማል። በትብብር ስም የራሳቸውን የአስተዳደር ስርዓትና ባህል ትተው የእነሱን እንዲቀበሉ ይደረጋል። አብረን እንደግ በሚል ሰበብ የሀብት ምዝበራው ቀጥሏል።

ለአፍሪካዊያን ግን አሳውን እንጅ አሳው እንዴት እንደሚጠመድ አያሳዩም። ሁሌም በህይወትና በሞት መካከል ኑሯቸውን እንዲገፉ ይደረጋል። የራሳቸውን ሀብት አልምተው እንዳይጠቀሙ በተለያየ መንገድ እንዲሰናከል ያደርጋሉ። ሀገሩንም ሆነ አህጉሩን ለማዘመን ወይም ለማሳደግ የሚፈልግን መሪ አምባ ገነን በማለት ጦር አዝምተው ከመንበረ ስልጣኑ ያሰናብቱታል። ለዚህ ትልቅ ማሳያ የምትሆነን የሰሜን አፍሪካዊቷ ሀገር ሊቢያ ነች። የውክልና ጦርነት በማወጅም የአቅም መለኪያ መፋለሚያ ሜዳም አድርገዋታል። ለእነሱ ሰብአዊነት ሽፋን እንጅ ደንታቸው አይደለም።

አፍሪካዊያን የራሳቸውን አቅም በራሳቸው ሃብት ለማሳደግ ሲሞክሩ ከባድ ጫና ይፈጠርባቸዋል። ለአብነትም ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሌት ተቀን ታትረዋል። ከግብጽ እስከ አሜሪካ፤ ከሱዳን እስከ አረብ ሃገራት፤ ከጸጥታው ምክርቤት እስከ አረብ ሊግ ድረስ ከፍተኛ ጫና አድርሰዋል። የራስን ሃብት አልምቶ መጠቀም በእነርሱ ዘንድ እንደ ወንጀልም ይቆጠራል። አፍሪካ ውስጥ ህይወት ቀያሪ ዘመን ተሻጋሪ ፕሮጀክቶች ግብ እንዳይመቱ አሻባሪ በማስታጠቅ እንዲደናቀፍ

ይደረጋል። በኦጋዴን ነዳጅ ለማውጣት በተሰማሩ በኢትዮጵያዊያን ዜጎችና የቻይና ዜጎችና ኩባንያ ላይ የደረሰው የሽብር ጥቃት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

በጥቅሉ አፍሪካ ያለ ምዕራባዊያን ይሁንታ የራሷን ሃበት አልምታ መጠቀም አትችልም። የአህጉሩን አንድነትና ሰላም ለማስጠበቅ የተቋቋመው የአፍሪካ ህብረት ጥርስ የሌለው አንበሳ ሆኖ ይገኛል። በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥም ወድቋል። የአፍሪካዊነቱን ሽፋን ተጠቅሞ የምዕራባዊያንን አጀንዳ አስፈፃሚ ሆኖ ይገኛል።

አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን የራስን እድል በራስ መወሰን በሚቻልበት፣ የምንተነፍሰውን አየር ሳይቀር እኛ ነን የምንሰጣችሁ ሲሉ ይደመጣሉ። እንደ እነ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ፣ ክዋሜ ኑክሬማ፣ ኔልሰን ማንዴላ፣ ሮበርት ሙጋቤ ወዘተ የነበሩበት አህጉር ሰፊ የሰው ኃይልና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት ይዞ ሁልጊዜ በርሃብ ይታመሳል። የእረስ በእርስ ጦርነቱም አላባራም። ከውክልና ጦርነት እስከ ሃብት ምዝበራ ድረስ ተጧጡፏል።

ሁሌም አጀንዳ እየተቀበሉ መተራመሱ እስከመቸ ድረስ ነው? የዳቦ ፍርፋሪ እየተቀበሉ ማንነትንና ክብርን ጥሎ የነጭ ፈረስ መሆንን እንዴትስ መምረጥ ተቻለ? አፍሪካ ራሷን ችላ እኩል ክብር የምታገኘውና እኩል እንደ ሌሎች መብቷና ድምጿ የሚከበረውስ መቼ ነው? መልሱን ለአንባቢያን ትቸዋለሁ። አበቃሁ። ሰላም!!!